ORIGINAL ARTICLE

The Formation of Geez Verbs and Semantically Relation

Senkoris Ayalew Kassa [1]

The main concept of this study focused on the etymological verbs in the Geez language, which is a new research on a few past verbs or root verbs the so called Qedamay Anqets (archetype door). It is classified into three pillars, of these mainly comparing the formation of verb scripts with semantic relation. Based on this, it tries to explore the secret relationship between one letter at the destination location, the mutual repetition of two letters and non-repeating letters. The writer also shows the verbs he used for illustration in a table and lists the characteristics of each word meaning or interpretation; and the relation between ideas and forms. Finally, it recommends further study is needed on thought related to Gee'z.

Keywords: *Verb, Semantic and Idea`s -relation*

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ፅንሰ ሐሳብ በግዕዝ ቋንቋ ውስጥ በሚገኙ ሥርወ ግሦች ላይ ያጠነጠነ ሲሆን ይኸውም በሀላፊ ጊዜ የተቀመጡና ቀዳማይ አንቀጽ እየተባሉ በሚጠሩ ውሱን ግሦች ላይ ያተኮረ አዲስ ምርምር ነው። ጥናቱም እነዚህን ግሦች በሦስት ጎራ ከፋፍሎ የተመለከተ ሲሆን በዋናነትም የግሦችን የሆህያት ቅርጽ ከትርጓሜው እሳቤ ጋር በማነጻጸር ፍቻዊ ዝምድናቸውን ያመላከተ ጥናት ነው። በዚህ መሠረትም ጥናቱ የአንድ ሆሄን በመድረሻ ቦታ የሚገኝ ተደጋጋሚ ተከታታይነትን፣ የሁለት ሆህያትን በቦታ መቀያየር የርእስ በርእስ ድግግሞሽንና የማይደጋገሙ ሆህያትን በማቅረብ በሐሳብ ደረጃ ከአተረጓጎም ስልት ጋር ያላቸውን ምሥጢራዊ ቁርኝት ለማስዳሰስ ሞክሯል። ለማሳያነት የተጠቀመባቸውን ግሦችም በሰንጠረዥ በማቅረብ የእያንዳንዳቸውን የቃላት አፈታት ወይም የአተረጓጉም ባሕርያትን እየዘረዘረ የሐሳብና የቅርጽ ተዛምዷቸውንም በምሳሌ አሳይቷል። በመጨረሻም ቢጠኑ መልካም ነው የሚላቸውን ሐሳቦች አንስቶ አስተያይቱን አስፍሯል።

ቁልፍ ቃላት፡- ግሥ፣ ሥነ ፍች፣ የሐሳብ ተዛምዶ

1 PhD Student in Philology Program at AAU and Instructor of Geez Language at University of Gondar, Ethiopia E-mail: senkorisayalew@gmail.com/ senkoris.ayalew@uog.edu.et

This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.

DOI: *https://doi.org/10.20372/erjssh.2022.0901.10*

መግቢያ

ኢትዮጵያ[2] በጥንቱ ዘመንም ቢሆን ታሪክ አላቸው ተብለው ከሚጠቀሱ ውስን ሀገራት መካከል ተመዛ የምትወጣ አንዷት የታሪክ ፈርጥ መሆኗን መዛግብት ሰንደዋል፤ የሚነበቡና የሚዳሰሱ የቅርስ መዛግብትም የመጀመሪያ መረጃ ምንጮቻችን ናቸው፡፡ እንደ ዘወትር ጸሎት ከሚነገሩላት ብቸኛ ስጦታዎቿ መካከል ደግሞ የግሏ ፊደልና ቁጥር፣ እንዲሁም የጽሕፈት ብልሃት[3] ና የዘመን አቆጣጠር[4] በግንባር ቀደም የሚነሡ የመፍቻ ቁልፎቿ ናቸው፡፡ መቼም ስለ ጽሕፈት ብልሃቷ ከተወሳ ላይቀር የመጻፊያ ቀመሮቿ ፊደላትም ለዚህ ጥናት የጀርባ አጥንት ናቸው፤ ምክንያቱም በጥናቱ ለሚቀርቡት የግዕዝ ግሦች ምሥረታ ሠሪዎቹም እነሱው ናቸውና፡፡ ከዚህም ባሻገር አሁን ላይ ለሚጠናው ለግዕዙ ሥነ ጽሑፍ[5] ም መሠረተ ጽሕፈት መሆናቸው የማይታበል ሐቅ ነው፡፡ እንደ ዓለም አቀፉ የጥናት መስመርም የግዕዝ ፊደላት/ ሆህያት[6] ከዘመን ዘመን የቅርጽ ለውጥ እየተደረገባቸው አድገው እዚህ እንደደረሱ ይነገርላቸዋል፡፡ ይሁንም እንጂ የግዕዝ ሆህያት እርስ በእርሳቸው ተጣምረው የአሁኑን የቃል ምሥረታ ወይም ሥርወ ግሣትን መቼ እንደመሠረቱ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ቅሉ አሁን የሚገኙት የግሥ ቅርጾች ግን በሥርዓት ተሰናስለውና ተውበው እንዲቀመጡ እንዲሁም ትርጉም እንዲሰጡ አስችሏቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም እነዚህ ግሦች ትርጉም አዘል ከመሆናቸው ባሻገር የሆህያት ድግግሞሽ ከፍቻዊ ብልሃት ጋር የማገናኘቱና የማመሳሰሉ ቁም ነገርም ተፈትሾበታል፡፡ምንም እንኳን በምሁራን ዘንድ ስለ ቋንቋ የሚሰጠው ብያኔ "ቋንቋ የወካይነት ወይም የስያሜና የተሰያሚነት ጉዳይ እንጂ ቃሉ ከመጠሪያው ጋር ተፈጥሯዊ ግንኙነት የለውም" ቢባልም ቅሉ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ሁሉም ቃላት ባይሆኑም ፣ውስን ግሦች ግን ከሚጠራው ወይም ከተሰየመው ነገር ጋር በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ ሲገናኙ ይታያሉ፡፡ እዚህ ላይ መሠመር ያለበት ነገር ቢኖር ሁሉም የግዕዝ ግሦች ማለት እንዳልሆነና የተወሰኑት ደግሞ ጥናት እንደሚያሻቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ስለ ቋንቋ ጥንተ አመጣጥ አንድ ሰሞን የተቀነቀነለት ድምጸ ቀድ መላምት /Onomatopoeia Theory/ ከዚህ እርሰ ጉዳይ ጋር የሚመሳሰል ቢመስልም ፍጹም የተራራቁና የማይገናኙ ሐሳባት ናቸው፡፡ ምክንያቱም የድምጸ ቀድ መላምት፣ "ቃላትን" ተኮረጁ ብሎ የሚያስበው በድምጽ ደረጃ ሲሆን ለምሳሌ "ፏፏቴ" የሚለው ቃል ውሃው ፏፏ ሲል ተሰምቶ ነው ቃሉ የተፈጠረ እንደማለት ይመስላል፡፡ በዚህ ጥናት የሚቀርበው ጉዳይ ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ድምጽን የማመሳሰል ሳይሆን የቃሉንና የትርጉሙን ግንኙነት ልሳናዊ በሆነ ፍልስፍና ማብራራት ነው፡፡

ይህ የግዕዝ የጥናት መስክም በሀገራችን ትኩረት ተነፍጎት በጥልቀት ባይመረመርም ቅሉ አንዳንድ የውጭም ሆኑ የሀገር ውስጥ ሰወች ግን ውስን በሚባል ደረጃ በመዝገበ ቃላት ቅርጽም ይሁን በዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ከሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ያለውን ግንኙነትም ይሁን የተውሶ ነገሮች ..ወዘተርፈ የሚሉ ጉዳዮችን ሳይነካኩ አልቀሩም፡፡ ለምሳሌ አንድ ኦገስት ዲልማን[7] የተባለ ጀርመናዊ Ethiopic[8]

2 ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን አኩሪ ታሪክ ያላትና የራሷ በሆነ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል የበለጸገች አገር መሆኗ የታወቀ ነው። ብሄረ ሰቦችን ያቀፈች አገር በመሆኗም የበርካታ ቋንቋዎችና ሥነ ቃሎች ባለቤት ናት። (የግዕዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ ንባቡ ከነትርጓሜው፤1980)

3 Writing was adopted by the Semites settled in Ethiopia – meaning the area between the northen highlands of the horn of Africa and the Red Sea, corresponding to the present-day states of Eritrea and Ethiopia the northen Tegray region of the latterin particular- as early as the first millennium BCE, much earlier than the date of the earliest surving manuscripts.(COMSt, 2015)

4 በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አስተምህሮ ውስጥ ሁል ጊዜ የሚታወሱና ደቀ መዛሙርቱም በጉባኤ ቤት ዘወትር ተምረዋቸውና ማስታወሻወችን መዝግበውባቸው እንዲሁም ለተተኪ ተማሪዎች የሚያስተላልፏቸው ልዩ የሆኑ የዘመን መቁጠሪያ መጻሕፍቶቻቸው፡- አቡሻክር፣ በሕረ ሐሳብ፣ መርሐ ዕውር... የተሰኙት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

5 የዛሬውን ኢትዮጵያዊ ትውልድ ከታሪኩና ከሀገሪቱ የጥንቱ ሥልጣኔ ጋር የሚያያዝው በግዕዝ ቋንቋ ቦይነት ከጥንቱ ዓለማችን እየተንዶለዶለ የመጣልን ቅርስ ነው። ኢትዮጵያንም ከጥንት አገሮች አንዷ ያደረጋት የመጻፍ ባህሏ ነው። ይህ ባህል ከሌላው አገር ባህል ጋርም አገናኝቷታል። ከራሷ በመነጨው ሥልጣኔ ላይ የሌላ ሀገሮች ሥልጣኔ እየቀዳች ያመጣችው በግዕዝ ቋንቋ ነው። የኢትዮጵያን የጥንት ታሪክ ብዙ ደራሲዎች ጽፈውልናል። ምንጫቸው በአብላጫው የግዕዝ መጻሕፍት ናቸው። (ጌታቸው ኀይሌ፣2008፣ ኒው ዮርክ)

6 የግዕዝ ፊደላት በቁጥር ሃያ ስድስት ሲሆኑ ፊደል የሚለው ቃልም "ፈደለ" ጻፈ" ከሚል የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ጽሑፍ ማለት ነው። (ለይኩን ብርሃኑ፣ የግዕዝ መማሪያ፣ 1998) 2ኛ. (ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ / መልከ ጼዴቅ/ ፣1963) "ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት" በሚለው መጽሐፋቸው፣ "ፊደል ብሂል መጽሔተ አእምሮ፣ ነቅዐ ጥበብ፣ መራሔ እውር፣ ጸያሔ ፍኖትና ርእሰ መጻሕፍት" ማለት ነው ይላሉ።

7 ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የግዕዝን ቋንቋ በመማር እንዲሁም ቅኔን በመቀኘት የኢትዮጵያውያን ውርስ የሆኑትን የግዕዝ መጻሕፍት በመመርመርና መዝገበ ቃላት በማዘጋጀት፣ የግዕዙን መጽሐፈ ሔኖክን ጨምሮ ብዙ መዛግብትን የመረመረ ጀርመናዊ ሰው ነው።

8 ኢቶፒክ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የውጭ ምሁራንና ጸሐፍት የሚግባቡበት ግዕዝ በሚለው ትርጉም ነው።

Grammar /የግዕዝ አገባብ/ በሚል ርእስ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰፈረ ሲሆን፣ ሁለተኛው እትም ደግሞ በካርል ቤዞልድ በ1899 እንደ ነጮቹ አቆጣጠር ተተርጉሞና ተሻሽሎ ታትሟል፡፡ የዚህ ታላቅ መጽሐፍ አዘጋጂም እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 1823-1894 በጥናት ላይ የቆየ ሲሆን ስለ ግዕዝ ቋንቋም መዝገበ ቃላትንና አገባባትን ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ ሌላው በቀዳሚነት የሚጠቀሰው በኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጎርጎርዮስ ርዳታ የመጀመሪያውን የግዕዝ ሰዋስው ያሳተመው ጀርመናዊው ኢዮብ ሉዶልፍ በ1661 ዓ.ም ቢሆንም የቃላትን የትርጉምን ዝምድና ግን በጥናቱ አልዳሰሰም፡፡ከዚህ ባለፈም በአማርኛውም ሆነ በግዕዙ መዝገበ ቃላት ዝግጅት የሚታወቀው ሌለኛው ጸሐፊ ደግሞ ወልፍ ሌስሉ ነው፡፡ ይህ ሰውም የግዕዝ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላትንና የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉማቸውን የያዘ መጽሐፍ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1987 ያዘጋጀ ስለሆም በ1991 ደግሞ እንደገና አሻሽሎ አሳትሞታል፡፡ ሌላው ስለ ግዕዝ መዝገበ ቃላት ሲነሣ ግንባር ቀደሙን ቦታ የሚይዙት ታላቁ ሀገር በቀል ሰው ሊቁ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ናቸው፡፡ “መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ” በተሰኘው መጽሐፍ ስለ ግዕዝ መዝገበ ቃላትና ተዛምዶ ስላላቸው ቋንቋዎች-እብራይስጥ፣ ዐረብኛውንና እንዲሁም ግሪኩን በማነጻጸርና አንዳንድ የግዕዝ ቃላትም ምንጫቸው ከየት እንደሆነ፣ ብዙ ጥናት ቢያሻውም በከፊል ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ይህ ሚዛን ደፊ መጽሐፍም በ1948 ዓ.ም ታትሞ ለትውልድ መገልገያ ሆኗል፡፡ ሌላው ስለ ግዕዝ “የጥንታዊ ግዕዝ መግቢያ” / Introduction to Classical Ethiopic/ በሚል ርእስ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1978 በቶማስ ኦ ላምዲን የጻፈው መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ የጽሕፈት ክፍልም በዋናነት የሚያጠነጥነው በግዕዙ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር[9] ላይ እንጂ የቃላት ምንነት ላይ ወይም ሥነ ፍቻዊ ሂደት ላይ አይደለም፡፡ ሌለኛው የግዕዝ አጥኚ ደግሞ ቤንደር የተሰኘው ስለቋንቋ ብዙ መዛግብትን ያሰፈረው ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ምሁርም በፈረንጆች አቆጣጠር በ1976 “ቋንቋ በኢትየጵያ” /language in Ethiopia/ በሚል ርእስ የጻፈ ሲሆን የግዕዙን ሥነ ድምጸ ልሳንና የድምጹን ተናጠላዊ ባሕርዩን ለማየት ሞክሯል፡፡ ይሁንም እንጂ ቃሉን ከትርጉሙ ጋር ያጠናበት ክፍል የለም፡፡ ሌላው “ጥንታዊ ግዕዝ” ወይም “Classical Ethiopic” በተሰኘ ርእስ በ1998 የጻፈ ስቴፈን ዊንገር ነው፡፡ ይህ ሰውም ስለ ግዕዝ ቋንቋ ሕግና ደንብ፣ ስለ አናባቢና ተነባቢ፣ እንዲሁም ስለዐረፍተ ነገር አወቃቀር… መዝግቧል፡፡ ይሁንም እንጂ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ግን ምንም ዐይነት ጥናት አላካሄደም፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም የግዕዙን ግሥ ቅርጽና የትርጉሙን ተዛምዶ ማሳየት ነው፡፡

- ♣ ውሱን የግዕዝን ቀዳማይ አንቀጽ/ሥርወ ግሥ ባሕርይ ማስቃኘት
- ♣ በቅርጽና በፍቻዊ አቻነት መካከል የሚታየውን ተግባራዊ አካሄድ ማስረዳት
- ♣ የተዛምዷቸውን ቁርኝት ማብራራት የሚሉት ዝርዝር ዓላማዎች ሲሆኑ፡-

እንዲሁም ጠቀሜታዎቹ ውስን የሚባሉ አይደሉም፡፡

- ♣ ለሌሎች ቤተሰብ ቋንቋዎች የጥናት በር ይከፍታል
- ♣ በቃልና በትርጉማዊ እሳቤ መካከል ያለውን ግንኙነት ያስተምራል
- ♣ ልዩ የሆኑትን ግሦች ለመመርመር ፍንጭ ይሰጣል
- ♣ የግዕዙን ቋንቋ[10] መዝገበ ቃላትን በመጠኑ በአማርኛው ያስተምራል፡፡

ከዚህ በመቀጠልም ማሳያ የሚሆኑ ውሱን ግሣትን አጥኝው በትንሽ ለማሳየት የሞከረ ሲሆን በሦስት መሥመር በሠንጠረዥ ውስጥ አስፍሯል፡፡ ይሁንም እንጂ ከታች የተዘረዘሩት የግዕዝ ግሦች[11] በሙሉ አለመሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከነዚህ ውስጥም አጥኚው ለትንተና የሚያስፈልጉትን ግሣት ብቻ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

---

9 የግዕዝ ቋንቋ አጥኚዎች ነን ባዮች፣ ስለ ዐረፍት ነገር አወቃቀሩ ሲጽፉም ሆነ ሲናገሩ ሁለት ዐይነት የአሰዳደር ስልት አለው ይሉናል። ይኸውም “ስም ሲደመር ግሥ ሲደመር ተሳቢና ግሥ ሲደመር ስም ሲደመር ተሳቢ” ማለታቸው ነው። ሌላ ዐይነት ለማሳየት፡- አንትሙሰ ከመ ሰብዕ ትመውቱ፤ አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ፤ ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ፤ ተንሥእ ተቀበለኒ ወርእይ፤ እግዚአብሔር ስቡሕ በቅዱሳኒሁ - ውእቱን ሲመረምር። ... በደንብ ቢጠና ዐረፍተ ነገራዊ አወቃቀሩ እነሱ የሚሉት ብቻ አይዶለም።

10 የግዕዙ ቋንቋ ሰዋስውና አገባብ እጅግ በጥንቃቄ ተመርምሮና ተዘጋጅቶ የተጻፈ ነው።በውስጡም ከእብራይስጥና ከፅርዕ ከሶርያና ከአረብ ቋንቋ ጋር የሚጋጠም አንዳንድ ቃል ይገኝበታል። ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣1918፣ መጽሐፈ ቅኔ የተሰኘው ታላቅ ቅርስ በልዑል ተፈሪ ማተሚያ ቤት ታትሟል።

11 የግዕዝ ግሥ ወይም ቀደማይ አንቀጽ ሁል ጊዜም መድረሻውን ግዕዝ ሆሄ ሲያደርግ ወይም በግዕዝ ሆሄ የሚጨርስ ሲሆን፣ መነሻ ሆህያቱን ግን አምስት ያደርጋል። እነሱም ግዕዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስና ሳብዕ ሲሆኑ ፣ በካዕብና በሣልስ ቀለማት ግን ቀደማይ አንቀጽ ፍጹም አይነሣም። በምሳሌ ሆህያቱን ከግሡ ጋር ለማሳየትም፡-ሰቀለ፣ባረከ፣ ሌወወ፣ ስሕከ፣ ሖረ... የሚሉትን ማየት ያስፈልጋል። አንድ አንድ ሊቃውንት እንደ ሚስማሙበት ሁሉ “ይቤ” አንድ በኃምስ የሚጨርስ ቀዳማይ አንቀጽ ነው አብሮ መነገር አለበት ሲሉ፣ አንድ አንድ የዘርፉ ምሁራን ደግሞ ይቤ ከ “ብህለ” የወጣ እንጂ እራሱን ችሎ ሊገሠሥ አይገባም ነበር ባይ ናቸው። በተጨማሪም “ይቤ” ነባር አንቀጽ ነው የሚሉ ሊቃውንትም ብዙዎች ናቸው።

ሠንጠረዥ "ሀ"	ሠንጠረዥ "ለ"	ሠንጠረዥ "ሐ"
1. ጠብለለ - ጠቀለለ	ነክነከ - ወዘወዘ	ነበረ - ተቀመጠ
2. ገልበበ - ሸፈነ	ዜርዜቀ - ነፋ	ዘበጠ - መታ
3. ቆርጰጰ - ቆረጠመ	አግደምደመ - አፋታለ	ፈቀደ - ወደደ
4. አርመመ - ዝም አለ	ከርከረ - ገረደፈ	አደመ አማረ
5. ቆረ/ ቆረረ - ቀዘቀዘ	ዘርዘረ - በተነ	ረገዘ - ወጋ
6. ሰደደ - አባረረ	ነስነሰ - ጎዘጎዘ/በተነ	ዘለፈ - ሰደበ
7. ደምሰሰ - አጠፋ/ደመሰሰ	አድለቅለቀ - ተነዋወጠ	ቆመ - ቆመ
8. ዳጎመመ - ናደ	ገብገበ - ወለወለ	ሤመ - ሾመ
9. ሐንቀቀ - አንሻተተ	ጣዕጥዐ - ቅልጥፍጥፍ አለ	ሰፍሐ - ዘረጋ
10. ገብሰሰ - አረጀ	ሳዕስዐ ቅልጥፍጥፍ አለ	ወለጠ - ለወጠ
11. መቀቀ - አንጣጣ	ቀጥቀጠ - ሰባበረ	ነጸረ - ዐየ
12. ጠንቀቀ - ጠነቀቀ	ለጽለጸ - መዘነ	ኀረየ - መረጠ
13. አክሞሰሰ - ፍግግግ ፍግግግ አለ	ለውለወ - ተውለበለበ	ገደፈ - ጣለ
14. ኤስከፐፐ - አረሰ	ፈልፈለ - መነጨ	ኖለወ - ጠበቀ
15. ለፈፈ - አዋጅ ነገረ	ደግደገ - ከሳ/ ማለዳ ሆነ/ነጋ	ነቀወ - ጮኸ
16. ሐፀ - ጎደለ	ተንተነ - ተፍገመገመ	ቃርሐ - ተኮሰ
17. ቀልጸጸ - ከመረ	ዘርዘረ - በተነ	ኀየለ - በረታ
18. ሰጠጠ - ቀደደ	ነፍነፈ - አካፋ	ጸገየ - አበበ
19. ደንዘዘ - ደነዘዘ	ጠብጠበ - ገረፈ	በረቀ - ብልጭ አለ
20. ጻሕየየ - አረመ	ቀጽቀጸ - ቆረጠመ	ቀነየ - ገዛ
21. ነደ - ነደደ	ተወነውኀ - ተመላለሰ	አንጦልዐ - ጋረደ
22. ከወወ - ቀለጠፈ	ተገህግሀ - ተከራከረ	መጠወ - ሰጠ
23. ሌወወ - ጠመጠመ	ነኀንኀ - ተትረፈረፈ	ከሠተ - ገለጠ
24. ሐልዘዘ - ፍሬ ያዘ/ አፈራ	አጽነሐንሐ - ወዘወዘ	ሰወረ - ደበቀ
25. አጽነነ - አዘነበለ	አንክሐክሐ - ፈተፈተ	ወሰከ - ጨመረ
26. ሐከከ - ተከራከረ	አንኮርኮረ - ተገለባበጠ	ያቀ - አወቀ
27. ቀብተተ - ነፋ	ደምደመ - አበጠረ	ቀተለ - ገደለ
28. የበበ - እልል አለ	አንበስበሰ - ተመላለሰ	ክህለ - ቻለ
29. አንበበ - አነበበ	በርበረ - በረበረ/ዘረፈ	ርኅበ - ተራበ
30. ሐበበ - ቆጠረ	አንጎርጎረ - አጉረመረመ	ኀደገ - ተወ
31. ረቀቀ - ጻፈ	አንጠብጠበ - አንጠባጠበ	ሠረወ - ነቀለ
32. ሠረረ - በረረ	ነክነከ - ወዘወዘ/ነቀነቀ/ኀለኀለ	ጸልመ - ጠቆረ
33. ሐረረ - ደረቀ	ነዝነዘ - ነዘነዘ	መተረ - ቆረጠ
34. ኀሠሠ - ፈለገ	ጎድጎደ - አንኳኳ/መታ	ሮፀ - ሮጠ
35. ኆሠሠ - ጠረገ	ገድገደ - ገረገደ	መርሐ - መራ
36. ገሠሠ - ዳሰሰ	አንገለገ - አከማቸ	ሰበረ - ሰበረ
37. አልኆሰሰ - አንሾካሾከ	ቀንጦሰጠ - ተሰለፈአሰለፈ	ወሀበ - ሰጠ
38. ጠንቀቀ - ጻፈ	ደፍደፈ - ለሰነ	ወረወ - ወረወረ
39. አንዛህለለ - ወላወለ	ጸፍጸፈ - ደረደረ/ጥፍጣፍ ሠራ	ተጸወነ - ተጠጋ
		አተወ - ገባ

ከላይ በሦስት ዐምድ በሠንጠረዥ ውስጥ ከተቀመጡት የቃላት ዝርዝር ወስጥ በ “ሀ” እና በ “ለ” ረድፍ ያሉት ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚለያዩ ሲሆኑ ከ “ሐ” መሥመር ግን ፍጹም የራቁ ናቸው፡፡ “ሀ” እና “ለ” ግን በሂደታዊ ወይም ሐሳብ ድግግሞሻዊነት ላይ ውስን መቀራረብ ይታይባቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሣትም እያንዳንዱን ቃል በመውሰድ በፍቻዊ ሂደታቸው ከሆህያት አቀማመጥ ጋር ያላቸውን ዝምድና አጥኚው እያነጻጸረ ለመተንተን ሞክሯል፡፡ለማሳሰብ ያህልም ስለ ግዕዝ ቀዳማይ አንቀጽ ግሦች አጥኚው ሲያስረዳ ሁሉም ግሦች በጥናቱ ይካተታሉ ማለት እንዳልሆነ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ ይህንን ባሕርይ የሚያሳዩም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ብቻም እንዳልሆኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተሰደሩት ቃላት ለማሳያነት ተሰነዱ እንጂ ተሚጠው የቀረቡ የግዕዝ ግሦች እንዳልሆኑም ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

የመተንተኛ ዘዴ

ከላይ በሠንጠረዥ ውስጥ የተካተቱትንም ሆነ ያልተካተቱትን የግዕዝ ግሥ ቃላት (ግሣት) በሙሉ መዘርዘርና ማብራራት ከጊዜም ሆነ ከጉልበት አንጻር አድካሚና ጠቃሚም ስላልሆነ፣ አጥኚው ጉዳዩን/ የጥናቱን ቁም ነገር ያሳዩልኛል ያላቸውን በሦስቱም ሠንጠረዥ “ሀ”፣ “ለ” እና “ሐ” ውስጥ የሚገኙ ዐሥር ዐሥር የግዕዝ ግሦችን እስከ አማርኛ ትርጉማቸው በመውሰድ ቅርጻቸውንና የሐሳብ ተዛምዷቸውን እያነጻጸረ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡

ትንተና አንድ፡- ሠንጠረዥ “ሀ” ተከታታይ ሆህያትን በመድረሻ የሚያሳዩ ግሦች

1. “**ጠብለለ**”[12] የሚለው የግዕዝ ቃል ፣ትርጉሙ “ጠቀለለ” ማለት ሲሆን ከግዕዙ ግሥ መድረሻ ላይም “ለለ” የሚሉ ተከታታይ ሆህያት ይገኙበታል፡፡ አማርኛውም ከግዕዙ ቃሉን ሲዋስ ማዕከላዊ ሆሄ የሆነች “ብ” ን ወደ ማዕከላዊ “ቀ” በመቀየር እንደ ግዕዙ ግሥ ቅሉ በአማርኛው ግሥ ላይም “ለለ” የሚሉ ተከታታይ ሆህያት በቃሉ መጨረሻ ይታዩበታል፡፡ይሁንም እንጂ የአጥኝው ዋና ቁም ነገር ውሱን የግዕዝ ግሦችን ባሕርያት ማሳየት ቢሆንም በትርጉም ጊዜ የሚጠቀመው ቋንቋ አማርኛ በመሆኑ ቃሉ እንዳለ ሲገኝ አብሮ ይዳስሳል፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ቁልፍ ጉዳይ የግዕዙ ግሥና የአማርኛው አቻዊ ትርጉሙ ሳይሆን ፣ በሆህያቱ ድግግሞሽና በትርጉሙ ሂደታዊ ድግግሞሽ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህንንም ለመረዳት “ጠቀለለ” የሚለውን ትርጉም ወስዶ መጠቅለል ምን ዐይነት ሂደት አለው ብሎ ማሰላሰልን ይጠይቃል፡ ፡ መጠቅለል ማለት አንድ ጊዜ አጥፎ መተው ማለት አይደለም፡፡ረጅም የሆነ ገመድን ወይም ሰንሰለትን አንድ ቀጭን እንጨት ይዞ በእንጨቷ ላይ ያንን ረጂም ገመድ ለተወሰነ ጊዜ በማዞር ደጋግሞ መደራረብን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ፍልስፍና በመነሣት “ለለ” የሚለው ሆሄ ስለተደጋገመ ትርጉሙም በአንድ ጊዜ ብቻ ታስቦ የሚተው አይደለም ትርጉማዊ ድግግሞሽ ወይም ሐሳባዊ ርዝመት ይታይበታል እንጂ፡፡

2. “**ገልበበ**” የሚለው የግዕዝ ቃልም ትርጉሙ “ሸፈነ” ማለት ሲሆን የመሸፈን እሳቤም አንድ ጊዜ እንደ መዝጋት ወይም በቅጽበት እንደመጋረድ አይደለም፡፡ለምሳሌ ተራራውን ጉም ሸፈነው ብንል እና በሂደት ብንመለከተው የቅጽበት ሥራ አይደለም ፤ ቀስ በቀስ ወደ መጋረድ የሚሄድ ነው እንጂ፡፡ ሌላው የጠጂን ገንቦ ወስደን መመልከት ያሻል ፡፡ አየር እንዳይወጣ የገንቦው አፍ ተሸፍኗል ከተባለ፣ አንድ እቃ ነገር ጣል ተደርጎበታል ማለት እንዳልሆነ ማሠብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም መሸፈን ሂደት ያለው ነገር ስለሆነ፡ ፡ ስለሆነም በግዕዙ የግሥ መድረሻ ላይ በተከታታይ የተገኙት “በበ” የተሰኙ ሆህያት ሂደትን ለማመልከት የተደረደሩ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ጥናታዊ እሳቤን ያሳያሉ፡፡

3. “**ቆርጸጸ**” የተሰኘው የግዕዝ ቃልም ወደ አማርኛው ሲተረጎም “ቆረጠመ” ማለት ሲሆን፣ ይህ የትርጉም እሣቤም መቆርጠም ማለት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ ማኘክንና ማድቀቅን የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም በግዕዙ ግሥ መድረሻ ላይ የሚገኙት ሁለት “ጸጸ” የተባሉ ተከታታይ ሆህያት ትርጓሜውን መሠረት አድርገው የተሰደሩ ናቸው የሚል የተመራማሪው ዕይታ ነው፡፡

4. “**አርመመ**”[13] የሚለው የግዕዝ ግሥ ትርጉሙም “ዝም አለ” ማለት ሲሆን የዝምታን እርዝመት እና እጥርት መለካት ከባድ ቢሆንም ቅሉ ዝምታ የሚለው እሳቤ ጊዜ ተወስዶ የሚተውና በጽሙና ማሰላሰልን

12 በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ፤ ውስተ ማሕፀነ ድንግል ኀደረ... የልደት ድጓ። (1988) በከብት በረት ተኛ በጨርቅ/ ጨርቆችም ተጠቀለለ.... ማለቱ ነው።

13 ናርምም እስመ ኢንክል ፈጽሞ (ውዳሴ ማርያም) ተናግሮ መጨረስ አንችልምና ዝም እንበል ሲል ነው።

የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን ሂደታዊ ሐሳብ ለማመልከት በግዕዙ የግሥ መድረሻ ላይ የተቀመጡ ተከታታይ “መመ” የተሰኙ ሁለት ሆህያት የትርጉሙ ማመላከቻ ናቸው እንዲባሉ አስችሏቸዋል፡፡

5. “**ቆረ/ ቆረረ**”[14] የሚለው የግዕዝ ሥርወ ግሥ ትረጉሙም “ቀዘቀዘ” ማለት ነው፡፡ በሐሳብ ደረጃ “ቀዘቀዘ” ወይም “ሞቀ” የሚለው ትርጉማዊ አንጽሮቱ በቅጽበት የሚተገበር ሁነት አይደለም፡፡ ጊዜ ወስዶና በሂደት የሚሆን ነገር ነው እንጂ፡፡ለምሳሌ የፈላን ውሃ ብንወስድ ወደ መቀዝቀዝ ሲጓዝ በአንዲት ፍጥነት አይደለም ቀስ ብሎ በመሳብ ወይም በመጎተት የሚሆን እንጂ፡፡ ስለሆነም በግዕዙ የግሥ ቃል መድረሻ ላይ የተሰደሩት “ረረ” የተሰኙት ሆህያት የጊዜን ርዝመት ወይም ሂደትን ለማመላከት የተሰደሩ ቁም ነገሮች ናቸው፡፡

6. “**ሰደደ**”[15] የሚለው የግዕዝ ግሥ ሲፈታ “አባረረ” ማለት ሲሆን ስለቃሉ በሐሳባችን የሚመላለሰው የትርጓሜ ክፍልም ተባራሪው በሩጫም ሆነ በዝግታ ከቦታው መሸሽን ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከቦታ ማፈግፈግን ያሳየናል፡፡ ከላይ እንዳነሣነው ነጥብ ሁሉ አሁንም በአማርኛው ትርጉም ጊዜም የሚታየው የሆሄ ድግግሞሽ ወይም “ረረ” የሚል ስደራ ይታያል፡፡ ስለሆነም የግዕዙ ቃል ወደ አማርኛው ሲተረጎም የትርጉሙን እሳቤ አማርኛውም አብሮ ይዞት ተሻግሯል ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ግዕዙም የተከታታይ ሆህያትን “ደደ” የተሰኙትን በመደርደር የትርጉሙን ሂደታዊነት በሆሄ ድግግሞሽ አሳይቷል፡፡

7. “**ሐከከ**” የሚለው የግዕዝ ቃል ፣ “ ተሟገተ/ ተከራከረ” የሚል ትርጉም ሲኖረው ፣ክርክርም የሚለው ጽንሰ ሐሳብም ተናገረ ከሚለው ፍቻዊ መሥመር የተለየ ነው፡፡ለምሳሌ ፡- ሁለት ሰዎች ተከራከሩ ብለን ብናስብ ፣ቁጭት በተሞላበት ወይም በፈቃድ ላይ የተመሠረተ የጠንከራ ምልልስ ውጤት መሆኑን እንመለከታለን፡፡ሌላው በዳኛ ፊት የቆሙ ሁለት ተጻራሪ ኀይሎችን ብንመለከት ፣ እኔ አሸንፍ እኔ አሸንፍ በሚል በእየተራ የሚያደርጉት ሰጣ ገባ የተሞላበት ሂደታዊ ሥርዓት ነው፡፡ የሂደቱ ጊዜ ከዚህ እስከዚህ ነው የሚባል ባይሆንም ቅሉ፤ ጊዜ ወስዶ ግን የተወሰነ ሂደትን እንደሚያልፍ ከትርጓሜያዊ ቅርጹ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በግዕዙ ግሥ መድረሻ ላይ ተከታትለው የተሰደሩ “ከከ” የተሰኙ ሆህያት የነገሩን ሂደታዊ ርዝመት ለማሳየት የመጡ ናቸው ማለት ነው፡፡

8. “**ሌወወ**”[16] የሚለው የግዕዝ ቃል ትርጓሜው “ጠመጠመ” ማለት ሲሆን፣ የጥምጠማን ተግባራዊ የአፈታት ሂደት ስንመለከት አንድ ጊዜ አዙሮ ማድረስን ብቻ የሚያስቃኝ አይደለም ፡፡ በቁጥር ይህን ያህል ጊዜ ይጠመጥማል ሳንል እንችላለን፡፡ ነገርግን ሻሽ በእራሱ ላይ ጠመጠመ፤ ነጠላ በአንገቱ ጠመጠመ፤ እባብ በእግሩ ተጠመጠመ… ወዘተርፈ እያልን ብንሄድ የመጠምጠም ርዝመቱ አንዱ ከአንዱ የተለየ የጊዜ ርዝመትንና እጥረትን ሊያስተናግድ ይችላል፡፡ ነገር ግን የጠመጠመ እሳቤ አንድ ጊዜ እንዳልሆነ በትርጉሙ መረዳት ይቻላል፡፡ስለሆነም በግዕዙ የግሥ መድረሻ ላይ የሚታዩት “ወወ” የተሰኙ ሆህያት ሂደታዊ ድግግሞሽን ለማሳየት የተቀነበቡ ናቸው እንዲባሉ ያስችላል፡፡ እዚህ ላይ ማንሣት የምፈልገው ነገር የግዕዙ ቃል ወደ አማርኛው ሲተረጎም ፣ የአማርኛው ቃልም በእራሱ የሆህያትን የእርስ በርስ ድግግሞሽ ያመላክታል፡ ፡ ይኸውም “ቀጠቀጠቀጠቀጠ… ዐይነት ይታይበታል፡፡ ከላይም ለማንሣት እንደሞከርሁት፣ የግዕዙ ቃል የሚያስተላልፈውን የድግግሞሽ ሂደት አማርኛውም በከፊል ወይም በሙሉ ወርሶት እንመለከታለን፡፡

9. “**ኀሠሠ**”[17] የተሰኘው የግዕዝ ቀዳማይ አንቀጽ ወደ አማርኛው ቋንቋ ሲመለስ ትርጉሙም “ፈለገ” ማለት ነው፡፡ “ፈለገ” የሚለውን የትርጉም እሳቤ ወደ አእምሯችን ቋት አስገበተን ስናሰላስል፣ መፈለግ

14 ወኮነ ከመ ማይ ቆሪር - እንደ ውሃ ቀዘቀዘ ማለቱ ነው።

15 ….. ተናዘዘ ብኪ አኮኑ ሕሊና ቀዳማይ አብ አመ እምገነቱ ተሰደ በኀዘን ዕፁብ - (መልክዐ ኪዳነ ምሕረት) ከገነት በተሰደደ ጊዜ ባንቺ ተጽናና። እንደ ማለት።

16 ሌዋውያን ሲል ካህናቱን ማመልከቱ ነው። ምክንያቱም ጠመጠመ ካለ፣ ጥምጣም ለካህናቱ አንድ መለያ ነው። በዘመነ ብሉይም ሌዋውያን ብሎ የሚያመለክተው የኦሪቱ ካህናት የነበሩበትን ዘመን መሆኑ ነው።

17 ኅሥሣ ለሰላም ወዴግና……. ኀሠሥኩ ወኢረከብኩ መካኖ… እያለ የኀሠሠን ቃል ምንነት ያሳያል። ሰላምን ተከተላት እንዲሁም ፈልጋት…. . ሲል ሁለተኛው ደግሞ ቦታውን ፈለግሁት ነገር ግን አላገኘሁትም . . ማለቱ ነው።በተጨማሪም መምህር ወልደ ሐና 1958 ዓ.ም ባሳተሙት የግዕዝ ሰዋስው፣ “ኀሠሠ” ሦስት ትርጉም አለው ብለው መጻሕፍትን በማስረጃነት በመጥቀስ ያብራራሉ። አንድኛ. ኀሠሠ -ፈለገ ሲሆን፣ “እስመ ኩሉ ዘሰአለ ይነሥእ ወዘሂ ኀሠሠ ይረክብ” እንዳለ ማቴ፣ 7፤8 ሁለተኛ ኀሠሠ- መረመረ የሚል ሲሆን “አኮኑ እግዚአብሔር እምተኀሠሦ ለዝንቱ” መዝ 44፤22 የሚል ሲሆን ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ፣ ኀሠሠ- ተከራከረ የሚል ነው። የዚህ ምስክርም፣ “ወኮነ ተኃሥሦ ማዕከለ አርዳኢሁ ለዮሐንስ ምስለ ይሁዳ” ዮሐ፤3፤25

ማለት አንድ ጊዜ አይቶ መተው ማለት እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ይህንን ጽነሰ ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳትም፣ አንድ ሰው ገብያ ውስጥ ወንድሙ ጠፍቶት የሚቃኝበትንና በመጻሕፍት ውስጥ ጥቅሶች ጠፍተውን የሚፈልግበትን የጊዜ ሂደት መመልከት ብቻ በቂ ነው፡፡ስለሆነም ይህ የግዕዝ ግሥ የሐሳብ ሂደታዊ ትርጓሜን ለማሳየት በመድረሻው ላይ "ሠሠ" የተሰኙ ተከታታይ ሆህያትን ሰድሯል፡፡

10. "**ጻሕየየ**" የሚለው የግዕዝ ቃል ወደ አማርኛው ቋንቋ ሲመለስም "አረመ" ማለት ነው፡፡ በሐሳብ ደረጃም አረመ የሚለውን ቃል ስንመለከት ነቀለ ከሚለው ይለያል፡፡ ምክንያቱም ነቀለ የሚለው ለአንድ ነገርም ሊሆን ይችላል፡፡ አረመ ከተባለ ግን የአንድ አርሶ አደርን ማሳና በአዝመራው መካከል የበቀሉ አረሞችን ማስታወስ ያሻል፡፡ ስለሆነም አራሚው በአዝመራው መሃል ገብቶ የሚያርም ከሆነ፣ በሂደት ብዙ እንክርዳዶችን እየለቀመና እየሰበሰበ ማስወገድን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የሚያርምበት የጊዜ እጥረትና እርዝመት አይታወቅ እንጂ በሂደት ማጥራትን ይመለከታል፡፡በዚህ ሁኔታም ትርጉማዊ እሳቤው፣ ሂደታዊ መሆኑን ለማሳየት "የየ" የተሰኙ ተከታታይ የመጨረሻ ሆህያት ተሰድረው ይታያሉ ማለት ነው፡፡

ትንተና ሁለት ፡-ሠንጠረዥ "ለ" ሁለት ሁለት የተለያዩ ሆህያትን በማቀላቀል የሚደጋግሙ ግሦች

የዚህ ትንተና ክፍል የሚያመለክተው ደግሞ እንደ "ሀ" የመጨረሻ ተከታታይና ተመሳሳይ ሆህያትን መደጋገም ሳይሆን ጥንድ ጥንድ ሆህያትን ቦታ በመቀያየር ሁለት ሁለት ጊዜ መደጋገም ነው፡፡ በዚህ የግሥ ቅርጽ ውስጥም የፊደላቱ ብዛት ዐራትና ከዚያ በላይ ናቸው፡፡

1. "**ነክነከ**" የሚለው የግዕዝ ግሥ ትርጉም "ወዘወዘ" ማለት ሲሆን፣ አማርኛውም በትርጉም እሳቤው እንዳለ ወስዶት ሲተረጎምም ድግግሞሽን ያስተናግዳል፡፡ ይሁንም እንጂ የግዕዙ ሆህያት "ነ" ሁለት ጊዜ፣ "ከ" ጊዜ በመደጋገማቸው የተነሣ የትርጓሜው ጽንሰ ሐሳብም ተደጋጋሚ እሳቤን ያስተናግዳል፡፡ ይህንን ነገር ለመረዳትም "ነክነክነክነክ… የሚለውን ፊደላዊ ስደራ ብቻ መመልከት በቂ ይሆናል፡፡ በአማርኛውም ወዘወዘወዘወዘወ… እያለ መሄዱን ማጤን ያሻል ፡፡ "ሀ" ላይ ያየነው ጉዳይ ከዚህኛው ክፍል የሚለይበት ዐቢይ ነገርም "ሀ" የጊዜ ሂደታዊ ርዝመትን ያመላከተ ሲሆን "ለ" ግን የሚያሳየው ሐሳባዊ ርዝመት ቢኖርም ቅሉ ዋና ቁም ነገሩ ግን ድግግሞሽን ማመላከት ነው፡፡

2. "**አግደምደመ**"[18] የሚለው የግዕዝ የግሥ ቃልም ወደ አማርኛው ቋንቋ ሲተረጎም "አፋታለ" የሚል ሲሆን ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ መረዳት የሚቻለውም "ደምደምደም…" እያለና እየደጋጋመ የሚነገረው የቃል ክፍል በትርጉም ጊዜ ያለውን የሐሳብ ድግግሞሽ የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቀላሉ ሐሳቡን ለመረዳትም ሆነ ለማስረዳት "አፋተለ" የሚለውን የአማርኛ ትርጉማዊ ቀመር ማሳየት ያሻልና፡፡ ለምሳሌ፡- እግሩን እያፋተለ ይጓዛል ከተባለ የማፋተል ሂደቱም እየተራ ነው፤ ወይም ድግግሞሻዊ ስልትን ያሳያል፡፡

3. "**ዘርዘረ**"[19] የሚለው የግዕዝ ግሥ ቃል ወደ አማርኛው ሲተረጎም " በተነ" ማለት ሲሆን ይህ የአበታተን ጽንሰ ሐሳብም ዘራ ለማለት ነው፡፡ ስለዚህ የመበተን ሂደትም አንድ ጊዜ ወይም አንድ ነገርን ብቻ አይደለም፤ እንዲሁም የተበተነው ጉዳይም አንድ ቅንጣት አይደለም፡፡ ብተናው ብዙ የሆኑ ነገሮችን ይይዛል እንጂ፡፡ የጥናቱ ግብም የዚህን ሐሳባዊ ድግግሞሽ ብልሃት ለማሳየት የግዕዙ ግሥ ሆህያት ሲቀነበቡ ድግግሞሽን ለማመልከት ሆህያቱ ተደጋግመው ተሰድረዋል ማለት ነው፡፡

4. "**ፈልፈለ**" የሚለው ቃል ወደ አማርኛው ሲመለስ ትርጉሙ "መነጨ" ማለት ነው፡፡ መነጨ የሚለውን ሐሳብ በቀላል መንገድ ለመረዳት ፉል ፉል/ ፊል ፊል የሚሉ ተግባራዊ ድግግሞሾቹን ከምንጩ ላይ

---

18 "አሌ ሎሙ እለ ያግደመድሙ እገሪሆሙ በጊዜ ጸሎት" የሚለው ብሂል ሲተረጎም፣ በጸሎት ጊዜ እግራቸውን የሚያፋትሉ ወዮላቸው እንደማለት ነው።

19 በአብዛኛው የሚባሉት የሥራይና የክታብ መዛግብት "…… . ወዘርዝር ምክሮሞ ለፀርየ ወለፀላእትየ ለገብርከ እገሌ" የሚሉ የመደምደሚያ ክፍሎች የተለመዱና ዘወትር የሚገኙ ክፍላተ ጸሎታት ናቸው። ትርጉሙም፡- "ለእኔን ለባሪያህ የጠላቶቼንና የምቀነኞቼን ምክራቸውን በትንባቸው" ማለቱ ነው፤

መመልከትን የሚጠይቅ ነው፡፡ስለሆነም መነጨ የሚለውን ድግግሞሻዊ ተግባር ለማመልከት የግዕዙ ቃልም “ፊልፊልፊልፊል….” የሚሉ ስደራዎችን አሳይቷል/ ወይም ተግባራዊ ድግግሞሽን በተደጋጋሚ ሆህያት ቀንብቦታል ማለት ነው፡፡

5. “**ነፍነፈ**” የሚለው የግሥ ቀዳማይ አንቀጽ ወደ አማርኛው ቃል ሲመለስ “ካፊያ አካፋ” የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ከዚህ ትርጉማዊ እሳቤም መረዳት የሚቻለው የካፊያን ድግግሞሽ ነው፡፡ ይህም ማለት ያካፋል የሚል ቃል ከተነሣ ከላይ ሚወርድ ድግግሞሻዊ የውሃ ነጠብጣብን ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም በአንድ ጊዜ መደፋትን አያመለክትም የነጠብጣቦችን መቆራረጥ ያሳያል እንጂ፡፡በዚህ ሁኔታም የግዕዙ የግሥ ቃል ሲቀነበብ የትርጓሜውን ድግግሞሽ ለማሳየት፣ ነፍነፍነፍነፍ..” የሚሉ እሳቤዎችን ተጠቅሟል እንደማለት ነው፡፡

6. “**አድለቅለቀ**”[20] የሚለው የግዕዝ ግሥ ትርጓሜም ወደ አማርኛው ሲመለስ “ተነዋወጠ”“አነዋወጠ” ማለት ሲሆን ፣ ይህንን ድግግሞሻዊ የትርጉም እሳቤ ለመረዳትም የጉርምራምን ጋጋታ፣ ምድር ከባድ ነገር ሲወድቅባት የሚፈጠረውን ድግግሞሻዊ ንዝረትና መነዋወጥን መረዳት በቂ ነው፡፡በዚህን ጊዜ የሚሰማው የንዝረት ሕግም ከውጫዊ የሰውነት ክፍላችን አልፎ ውስጣዊ ክፍሎቻችንን ሲያንቀጠቅጣቸው ይሰማናል፡፡ ስለሆነም ይህንን ድግግሞሻዊ የትርጉም ሐሳብ ለመረዳት በግዕዙ የግሥ ክፍል ላይ “ለቅለቅለቅ…” የሚል ሆሄያዊ ድግግሞሽን ያመላክታል፡፡

7. “**ደምደመ**” የሚለው የግዕዝ ሥርወ ግሥ ትርጓሜው ወደ አማርኛ ሲቀየር “አበጠረ” ማለት ሲሆን የማበጠርን የአተረጓጉም እሳቤንም ስንመለከት ጸጉርን በማበጠሪያ መከፍከፍን ያመለክታል፡፡ ይህ ተግባርም በአንድ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን በማበጠሪያ ጸጉርን ደጋግሞ ደጋግሞ መንቀስን ያመለክታል፡፡ ይህንን የድግግሞሽ ሕግን ለማሳየትም “ደምደምደም..”የሚሉ የሆህያትን ድግግሞሽ አስተናግዷል፡፡

8. “**አንበስበሰ**”[21] የሚለው የግዕዝ ሥርው “ተመላለሰ” የሚለውን የአማርኛ ጥሬ ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን፣መመላለስም አንድ ሂደት ብቻ አይደለም የዓመታትን፣ የዕለታትን፣ የቀናትን እንዲሁም ዘሃ የሚዘጋ ሰውን ዑደት መመልከት ብቻ ተመላለሰ ለሚለው ስነፍቻዊ ድግግሞሽ አስረጂ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ዋና ቁም ነገርም “በስበስበስበስ….” የሚሉ የሆህያት ሁለት ሁለት ጊዜ ድግግሞሾች በትርጉም ጊዜ የምንመለከተውን ሐሳባዊ የፍች ድግግሞሽን ለማመልከት የተሰነዱ ናቸው ማለት ነው፡፡

9. “**ጸፍጸፈ**”[22] የሚለው የግዕዝ ግሥ የአማርኛ አቻ ትርጉሙ “ደረደረ/ጥፍጣፍ ሠራ” ማለት ሲሆን፣ ደረደረ የሚለው በራሱ የአማርኛው ቃል ትርጉማዊ እሳቤውን ለማሳየት እንደ ግዕዙ ቃል ሁሉ ተደጋግሟል፡ ፡ ለማሳየት የተፈለገው ቁም ነገርም ርብራብ ሠራ ሲባል የሚደረደረው ነገር አንድ እንዳልሆነ በትርጉሙ መረዳት ይቻላል፡፡ ብዙ ነገሮችም በተመሳሳይ ሁኔታ መሰደራቸውን የሚጠቁም ፍቻዊ አቋም ያስዳስሳል፡ ፡ ይህን ተደጋጋሚ ትርጉማዊ እሳቤ ለማመልከትም “ጸፍጸፍጸፍጸፍ…”እያሉ የሚደጋገሙ የግዕዙን ግሥ ሆህያትን ለማስረጃነት አጥኚው አቅርቧል፡፡

10. “**ቀጥቀጠ**”[23] የሚለው የግዕዝ ግሥ ለአማርኛውም ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን ትርጉሙም “ሰባበረ/ ቀጠቀጠ” የሚል ነው፡፡ የዚህ ጽንሰ ሐሳብም ቀጠቀጠ ሲባል አንድ ጊዜ መታ ማለት እንዳልሆነ ትርጉማዊ እሳቤው ይመሰክራል፡፡ ብረት ቀጠቀጠ ብንል አንድ ጊዜ መትቶ መተውን አያመለክትም፡፡ ይልቁንስ ጊዜ ወስዶ መደጋገምን ፍቻዊ ሐሳቡ ያስረዳል፡፡ ተግባራዊነቱን ለማመልከትም “ቀጥቀጥቀጥቀጥ….” የሚሉ ቃላት የሐሳብ ድግግሞሽን ለማመልከት የሆህያትን ድግግሞሽ በማስረጃነት ተሰድረዋል፡፡

---

20 አድለቅለቃ ለምድር ወሐካ (መዝሙረ ዳዊት)......ንባቡ ሲጠብቅ- ምድርን አነዋወጥሃት እንዲሁም ነቀነቅሃት እንደማለት ነው። ሲላላ ደግሞ- ምድርን አነዋወጣት እንዲሆም ነቀነቃት ማለቱ ነው።

21 “ወያንበሰብሱ ደመናት እምዐረብ ወሠርቅ” ይላል። (መልክዐ ኢየሱስ) ሲተረጎምም- ደመናት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ወይም ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ይመላለሳሉ ማለቱ ነው።

22 “አዘብ ወሲላስ ወጼናታም የዐውዱ ጸፍጸፈ ቤትየ” ይላል።(መሐልየ መሐልይ) ሲተረጎመም- አዛብ፣ ሲላስና ጺናታም የተባሉ ጥሩ መዓዛ ያላቸው የቤቴን ጽፍጻፍ/ ርብራብ ይከባሉ እንደማለት ነው።

23 “ቀጥቅጥ መዝራዕቶ ለኀጥእ ወለእኩይ”...”ወቀጥቀጠ መናስግተ ዘሐጺን” “ወቀጥቀጠቶ ለዳጎን....” ወዘተ የሚሉት መዛግብት ሁሉ ስለ ነገሩ መሰባበር የሚያመለክቱ ናቸው።

ትንተና ሦስት፡- ሠንጠረዥ "ሐ" ምንም ድግግሞሽ የማይታይባው ግሦች ባሕርያት

በዚህኛው የትንተና ክፍል የምንመለከተው ደግሞ ምንም ዐይነት የሆህያት ድግግሞሽ የማያካሂዱ የግሥ ክፍሎችና ትርጉማቸውም ሂደትንና ድግግሞሽን የማይቃኙትን ይሆናል፡፡ እነዚህን መዘርዘር ያስፈለገበት ምክንያትም ከላይ ከተጠቀሱት "ሀ" እና "ለ"ን ስለማይመስሉና ሐሳባዊ ወይም ሆሄያዊ ድግግሞሽን ስለማያካትቱ ለማሳያነት ነው፡፡

1. "**ነበረ**"[24] የሚለው የግዕዝ ቃል ትርጉሙም "ተቀመጠ" ማለት ነው፡፡ የተቀመጠን ትርጉማዊ እሳቤን ስንረዳም ፣ መቀመጥ የሚለው ሐሳብም ጊዜ የሚወስድ ወይም ድግግሞሽ የሚታይበት ሳይሆን በአንድ ጊዜ የሚከወን ወይም ሥነ ፍቻዊ ርዝመት የማይታይበት ቅጽበታዊ ቀመር ነው፡፡

2. "**ዘበጠ**" የሚለው የግዕዝ ቃልም ወደ አማርኛው ሲመለስ "መታ" ማለት ሲሆን እሳቤውም አንድ ጊዜ ነው፡ ፡ ደበደበ ፣ቀጠቀጠ፣ ከተከተ… እንደሚለው ድግግሞሻዊ ትርጉም የለውም፡፡ ስለሆነም ቃሉ የሚያመለክተው አንድ ቅጽበታዊ ክንውንን በመሆኑ የግዕዙ ግሥም ምንም ዐይነት የፊደላት ድግግሞሽን አላስተናገደም፡፡

3. "**ፈቀደ**"[25] የሚለው የግዕዝ ቀዳማይ አንቀጽም በአማርኛ "ወደደ" ማለት ሲሆን የወደደን ድግግሞሽና ሂደታዊነትን በግሡ ሆህያትም ሆነ በትርጉማዊ እሳቤው አንመለከትም፡፡ ስለሆነም ተናጠላዊ ሆህያት ስለተቀመጡ ድግሞሽን አላሳየንም እንደማለት ነው፡፡

4. "**አደመ**"[26] የሚለው ዘወትራዊ ቃልም ትርጉሙ "አማረ" ማለት ሲሆን ይህንን ትርጉማዊ እሳቤ ስናሰላስለው ከፊደልም ሆነ ከትርጉም ላይ ድግግሞሻዊ ስልትን አንመለከትም፡፡ ስለዚህ የሆህያቱ ድርደራም የትርጉሙ ሂደትም ነጠላና ቅጽበታዊ ነው ማለት ነው፡፡

5. "**ረገዘ**"[27] የሚለው የግዕዝ ግሥ ላልቶ ሲነበብ የአማርኛ ትርጉሙም "ወጋ" ማለት ነው፡፡ የዚህ ትርጉማዊ እሳቤም ድግግሞሻዊ ወይንም ሂደታዊ አይደለም፡፡ ምናልባትም የሆህያት አለመደጋገም የትርጉም ሐሳቡም ቅጽበታዊ እይታ እንዲታይበት አድርጎት ሊሆን ይችላል፡፡
6. "ዘለፈ" የሚለው የግዕዝ ቃል ወደ አማርኛው ሲተረጎም "ሰደበ" ማለት ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የትርጉም ወይም የሆህያት አለመደጋገምን ሲሆን ይህ የሆነበት ምክንያትም እንደ አጥኚው ሐሳብ በግሡ ላይ የፊደላት ድግግሞሽ ባለመታየቱ ነው ማለት ነው፡፡

7. "**ቆመ**"[28] የሚለው የግዕዝ ቃል በአማርኛውም እራሱን የሚደግም ወይም እዛው በተመሳሳይ "ቆመ" ማለት ሲሆን ከትርጉማዊ እሳቤው መረዳት የሚቻለውም ተደጋጋሚነት ወይም ሂደታዊነትን የሚያመላክት አለመሆኑን ነው፡፡በዚህም ምክንያት ይህ ቆመ/ ቀወመ የተሰኘ ግሥ ባለመደጋገሙ ትርጉማዊ እሳቤውም ነጠላ እንዲሆን አድርጎታል ማለት ነው፡፡

8. "**ከሠተ**"[29] የሚለው የግዕዝ ግሥ ወደ አማርኛው ሲተረጎም "ገለጠ" ማለት ሲሆን ይህ እሳቤም በአንድ ጊዜ የሚተገበር ነገር እንጂ ሂደታዊ ወይም ድግግሞሻዊ አለመሆኑን ከቃሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆለም የአጥኚው ዋና ዐላማ ከሠተ የሚለው ሥርወ ግሥ ሆህያቱ ስላልተደጋገሙ ትርጉማዊ እሳቤውም ነጣላ ነው ለማለት ማሳያው አድርጓል፡፡

9. "**ሰወረ**"[30] የሚለው የግዕዝ ግሥም ወደ አማርኛው ሲመለስ "ደበቀ" ማለት ነው ፡፡ ይህም አንድ

---

24 "ወዘኢነበረ ውስተ መንበረ መስተሣልቃን" "ወነበርኩ ውስተ ዐውደ ከንቱ" "ነበረ በገዳም ወበአታት" ወንበሩ ድልዋኒክሙ" . . ወዘተ የሚሉ አረፍተ ነገራት ስለመቀመጥ የሚናገሩ ናቸው።

25 "ፈቀደ እግዚእ ያግዕዞ ለአዳም" የሚለው ሐረግ መውደድን የሚያመለክት ሰነድ ነው።

26 "አዳም ቆማ ለማርያም ወክሣዳ ከመ አርማስቆስ…" "አዳም ወሠናይት . ." የሚሉ ነገሮች ሁሉ ማማርን የሚያመላክቱ ሐረጋት ናቸው።

27 "ወረገዘዎ ገቦሁ …" ወጋ የሚላውን አጽንኦት ለመስጠት የመጣ ሐረግ ነው።

28 "ቆመ" የሚለው ቃል በምስክር ብዙ ዐይነት ትረጉም ያለው ቃል ሲሆን፣ የመጀመሪያው እንደ አማርኛው እዛው ሳይቀየር "ቀመ" የሚል ነው። "ኀለፈ ክረምት ቆመ በረከት" ሲል ተተካ ማለቱ ነው። ሌላው - "እግዚአብሔር ቆመ ውስተ ማኅበረ አማልክት" ሲል -ፈረደ ማለቱ ነው።

29 "ከሠተ ለነ ብርሃነ ዜናሁ ለመድኅኒነ" የሚለው ዐረፍተ ነገርም ገለጠ የሚለውን ትርጉም ለማመላከት ነው።

30 "መንጦላዕተ ደመና ሰወራ" መደበቅን የሚሳይ ሐረግ ነው።

ቅጽበታዊ የትርጉም እሳቤን የያዘ ነው፡፡ በግሡ ውስጥ ተደጋጋሚ ሆህያት ባለመኖራቸው የትርጉም እሳቤው ነጠላና የማይደጋገም እንዲሁም በሂደት ጊዜን የማያቃጥል ነው ማለት ይቻላል፡፡

10. "**ቀተለ**"[31] የሚለው ዘወትራዊ ቃልም ወደ አማርኛው ሲመለስ "ገደለ" ማለት ሲሆን የገደላ ሁኔታም ከትርጉም እሳቤ እንደምንረዳው ቅጽበታዊ ነው እንጂ ሂደታዊ ወይም ድግግሞሻዊ አይደለም፡፡ ይህንን የማይደጋገም ሁነት ለማስረዳትም በግዕዙ ግሥ ላይ የሚገኙት የሆህያት ስድሮች እርስ በርሳቸው አልተደጋገሙም ማለት ነው፡፡

መደምደሚያና አስተያየት

መደምደሚያ

በሦስቱም ሰንጠረዦች ውስጥ ከሚገኙ የግዕዝ ግሦች ውስጥ ዐሥር ዐሥር በመውሰድ ሐሳቤን ያሳኩልኛል ያላቸውን አጥኚው የተነተነ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የተዳሰሱ ጉዳዮችም የትርጉማዊ እሳቤ ሂደት፣ የትርጉማዊ እሳቤ ድግግሞሽና የማይደጋገሙ ትርጉማዊ እሳቤዎች ናቸው፡፡ እንዚህን እሳቤዎች በተግባር ለማስረዳትም በግሥ መድረሻ የሁለት ሆህያት ድግግሞሽ፡- ሐሳባዊ ሂደትን በግሡ ውስጥ የሚደጋገሙ ሁለት ሁለት ሆህያት ደግሞ ፡- ሐሳባዊ ድግግሞሽን፣እንዲሁም በግሡ ውስጥ የማይደጋገሙ ሆህያት፡- የሐሳብ አለመደጋገምን ተመልክተንባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከግዕዙ ጎን ለጎን የሚገኙ የአማርኛ ግሥ የሆህያትን ድግግሞሽና ሐሳቦችንም ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

አስተያየት

የግዕዙ ቋንቋ ቃላት፣ ሆህያት፣የዕርባታ ስልት፣የዐረፍተ ነገር አወቃቀር.. ወዘተርፈ በደንብ ያልታዩና ያልተዳሰሱ የጥናት ሜዳዎች ናቸውና ትኩረት ተሰጥቷቸው ቢመረመሩ የተለየ እይታን በአዲስ መንገድ የሚያበሥሩ ናቸው፡፡ከግዕዙ በተጨማሪም አማርኛው ውስጥ የሚታዩ የግዕዙ ቋንቋ ባሕርያት ሲከሠቱ ተመልክቻለሁ፡፡በእርግጥ አማርኛው ላይ የሰዋስዉ ሊቃውንት፡-መርሰዔ ኀዘን[32] ፣ ፕሮፌሰር ባየ[33] ና ፕሮፌሰር ጌታሁን[34] …..ወዘተ ቢያጠኑትም ቅሉ ከግዕዙ ጋር የሚያገናኘውን ጉዳይ ግን አልዳሰሱትም ባይ ነኝ፡፡ ይሁንም እንጂ ከላይ እንደተመለከትናቸው የግዕዝ ግሦች አማርኛውም እንዲሁ የሂደትን፣ የድግግሞሽንና ያለመደጋገምን ሁነቶች በግሥም ሆነ በሐሳብ ጉዳዩን ያመለክተናል፡፡ ይህንን ተመሳስሎሻዊ ቁም ነገር ለማስረዳትም በሰንጠረዥ ውስጥ ውስን የአማርኛ ግሦችን ማሳየት ተገቢ ነው[35] ፡፡ እዚህ ላይ ሊሠመርበት የሚገባ ቁልፍ ጉዳይ፣ ሁሉም ግሦች ይህንን ባሕርይ ይወርሳሉ ማለት አይደለም፡፡ ከግዕዙ ግሥ ላይ ያስቀመጥሁት ማስጠንቀቂያ ለአማርኛውም ያገለግላል፡፡

ሂደታዊ፣ድግግሞሻዊና የማይደጋገሙ የአማርኛ ግሥ ምሳሌያት፡-

ሂደታዊ ግሦች	ድግግሻዊ ግሦች	የማይደጋገሙ ግሦች
መዘዘ	ዘለዘለ	ተቀመጠ
መጠጠ	ተመተመ	ነደፈ
ዳሠሠ	ቀጠቀጠ	ወጋ
ቀፈፈ	ገዘገዘ	ሞተ
ቀመመ	ሰቀሰቀ	ዐየ

31 "ወቀተለ ነገሥተ ጽኑዓነ" መግደልን የሚያመለክት መጽሐፋዊ ሐረግ ነው።

32 በ1948 የታተመ የአማርኛ ሰዋስው በስፋት የሚቃኝበት ቀዳሚ መጽሐፍን ለተመራማሪና ለተማሪ እንዲሁም ለአስተማሪ አበርክተዋል።

33 በሀገራችን ብዙ ጥናትና ምርምርን ያካሄዱ እውቅ ምሁር ሲሆኑ በ2002ም ሌላ የተሸሻለ የአማርኛ ሰዋስው "አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው" በሚል ስያሜ አበርክተዋል።

34 በ1989ም ጌታሁን፣ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ፣ በቀላል አቀራረብ በሚል በአብዛኛው የባየን ሐሳብ የተሸከመ የሰዋስው መጽሐፍ አበርክተዋል።

35 አጥኝው ማንሳት የሚፈልገው አንድ ቁልፍ ጉዳይ የግዕዙ የእግር ድግግሞሽ ስላለው አማርኛውም በሙሉ እቻ ትርጉም ይኖረዋል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

እነዚህንና የመሳሰሉትን ቃላት በመውሰድ የበለጠ ማጥናት እንደሚቻል የአጥኚው ግላዊ መልእክት ነው። እንዲሁም የአማርኛው ቋንቋ ቃላትን በብዛት የሚጠቀመው ከግዕዙ ሲሆን ተዛምዷቸውም ቀላል የማይባል በመሆኑ የግዕዙ ቃል በተጠና ቁጥር የአማርኛው ቃልም አብሮ የመከሠት እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው።

References

Habta Mariam Warqnah. (1969). *Ancient Ethiopian Education System*. Addis Ababa)

Layikun Birhanu. (1969). *Learning of Geez*. (first edition) Washington DC, United States of America.

Marsie Hazan walda Qirqos. (1948). *Amharic Grammar*. Addis Ababa, Artistic Printing)

……….*Book of Antiphony*. (1980). Addis Ababa)

Baye Yimam. (2002). *Short and easy Amharic Grammar*. Addis Ababa.

Hiruy Walda Silase. (1918). *Book of Ethiopic Poem*. Liul Tafari Makonen Printing.

AELC.(1980). *The Ethiopic Poems of art heritage, the reading and with the interpretation*. Birhan and Salam Printing.

Kidanawald Kifle. (1948). Book of Grammar and new dictionery. Addis Ababa: Artistic Printing.

Walda Hana Taklahaymanot. (1958). *Book of Grammar*. Birhan and Salam Printing.

….. .(1961). *Half of 19th c commentary, praise of St. Mary*. Tasfa Gabra Sillase printing.

………(1955). *Psalm Commentary*. Birhan and Salam Printing.

Getahun Amare. (1989). *Modern Amharic Grammar with easiest approach.* Addis Ababa trading printing.

Getachew Haile. (2008). Geʽez in easy way. Revised and flourished edition, New York Printing.

Bender, M. L., (1976). *Language in Ethiopia*: Londen: Oxford University press.

COMSt, (2015). *Comparative Oriental Manuscript Studie an Introduction, Tradition*, Hamburg

Dillmann, August, (1907). *Ethiopic Grammar. Trans.James A. Crichton.* London: Wiliams and

Nargate

Leslau, Walf, (1991). *Comparative Dictionary of Geez (Classical Ethiopic*). Otto harrassowitz, Wiesbaden.